አገልጋይና ስልጡን ሲቪል ሰርቪስ ግንባታ የትኩረት አጀንዳዎች

ለመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን አመራሮችና ሠራተኞች ግንዛቤ ማስጨበጫ ሰነድ

ታህሳስ 2017 ዓ.ም

<u>አዲስ አበባ</u>

መግቢያ

በዓላማችን ዘመናዊ የሲቪል ሰርቪስ አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት የተጀመረው በ18ኛው ክፍለ ዘመን ከኢንዱስትሪ አብዮት መጀመር ጋር ተያይዞ መሆኑን የታሪክ ድርሳናት ያሳያሉ። ከ19ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ የሰው ኃይል ስምሪት እና አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት ሳይንሳዊ እና ዘመናዊ እንዲሆን "የማክስ ቄበር ቢሮክራሲ ንድፈ ሃሳብ" ትልቅ አስተዋጽኦ ማድረጉን አብዛኛው ምሁራን ይስማሙበታል።

በ20ኛው ክፍለ ዘመን የኮምፒውተር እና የመረጃ መረብ ቴክኖሎጂ በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ በመምጣቱና በቅርብ ጊዜ ደግሞ የሰው ልጅ ከሰው ሰራሽ አስተውሎት (Artificial Intelligence) ጋር በመቀናጀት ሥራዎችን ማቀላጠፍ የሚችልበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ከመቼውም በላቀ አኳኋን የሲቪል ሰርቪስ አገልግሎት ተቋማትም ቅንጅት በመፍጠር እና በቴክኖሎጂ አማካይነት ዜጎች በሰባቱም ቀናት ሃያ አራት ሰዓት የተሳለጠ አገልግሎት ማግኘት የሚችሉበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል።

በኢትዮጵያ የመንግስት አስተዳደር (Public adiministration) የረዥም ጊዜ ታሪክ ያለው ቢሆንም የሲቪል ሰርቪስ ዘመናዊ አሠራር የተጀመረው ግን በ1900 ዓ.ም መሆኑን ጠናቶች ያስረዳሉ። አሰራሩም ከሃይማኖት፣ ከዝምድና፣ ከሙስና እና ከኋላቀር ትስስት ሳይላቀቅ ረጅም ዓመታትን አስቆጥሯል። የመጀመሪያው የሲቪል ሰርቪስ የማሻሻል እርምጃ ከ1950ዎቹ ጀምሮ ሥራ ላይ ለማዋል ጥረት የተደረገ ሲሆን በወቅቱ የሲቪል ሰርቪሱን አሠራር ዘመናዊና በህግ የሚመራ ለማድረግ አንዳንድ የለውጥ እርምጃዎች መወሰዳቸው ለሲቪል ሰርቪሱ እድገት መሠረት ጥሎ አልፏል። በኢትየጵያ የተደረገው ሌላኛው መሠረታዊ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች በተቀረፁበት ወቅት ነበር። ከዚያን ጊዜ አንስቶ ባለፉት ሁለት አስርተ ዓመታት በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ የተለያዩ የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራሞች እና የአሰራር ሥርዓቶች ተግባራዊ ተደርገዋል።

ሆኖም በዚህ ሁሉ ጊዜ እከ2016 ዓ.ም ሲቪል ሰርቪሱን ወደ ላቀ የእድገት ደረጃ የሚወስድ ሁሉም የተስማማበትና በመንግስት የፀደቀ ራሱን የቻለ የፖሊሲ ማዕቀፍ ሳይወጣ እስከ አሁን ድረስ ሲቪል ሰርቪሱ በአገራዊ የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ የልማት እድገት ውስጥ የማይተካ ሚና ያለው ነው። ጠንካራ መንግሥት ወይም ጠንካራ የክልል አስተዳደር ወይም ጠንካራ ሚኒስቴር መ/ቤት ወይም በጥቅሉ ጠንካራ ተቋም ስንል ጠንካራ ሲቪል ሰርቪስ አለው

ማለታችን ነው። በመሆኑም ጠንካራ የመፈፀም አቅም ያለው መንግስት እንዲኖር እና ዘርፎች ምርታማነታቸው እንዲያረጋግጡ ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር በማድረግ አገሪቱን ወደ እድገትና ብልጽግና ለማሸጋገር እንዲሁም ዘመናዊ ማህበረሰብ ብሎም ጠንካራ ሀገረመንግስት ለመፍጠር ከፍተኛ ድርሻ አለው በእስካሁኑ ሂደት ሲቪል ሰርቪሱን ለማሻሻል ጥረቶች ቢደረጉም በመሠረታዊነት ከችግር አዙሪት በማላቀቅ በሚፈለገው ደረጃ ላይ ማድረስ ግን አልተቻለም።

በሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ አሁን እየተስተዋሉ ያሉ መሠረታዊ ክፍተቶች የሚያመላክቱት የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ አሁን ባለበት ቁመናው የመንግስት እና የህዝቡን የለውጥ ፍላጎት ሊያሳካ በሚያስችል ይዞታ ላይ አለመሆኑን የሚያስገነዝብ ነው። በመሆኑም የመንግስት ተቋማትን የመፈፀም ብቃት በማጎልበት፣ የዜጎችን ፍላጎት የሚያረካ፣ ዓለም ወደ ደረሰበት የዕድገት ደረጃ ሊያሸጋግር የሚያስችል ግልጽ የሆነ የመንግስት አገልግሎትና አስተዳደር ፖሊሲ እና የትግበራ ስትራቴጂ በመንደፍና ተግባራዊ እንቅስቃሴ በማድረግ ችግሮቹን በጊዜ የለንም መንፈስ (sense of urgency) እየፈቱ መሄድ አስገዳጅ ሆኖ ተገኝቷል። በዚሁ መሠረት አዲስ በጸደቀው የሲቪል ሰርቪስ ፖሊሲ የተቀመጡ የእርብርብ አጀንዳዎች ለውይይት መነሻ ይሁኑ ዘንድ እንደሚከተለው ተዳሰዋል።

1. ብቃት ያለው ገቢር ነበብ አመራር ለጠንካራ ሲቪል ሰርቪስ ግንባታ

በሀገራችን ቀደም ሲል የተካሄዱ የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ እንቅስቃሴዎች የሚጠበቀውን ውጤት ማስመዝገብ ያልቻሉበት ሁለት መሠረታዊ ምክንያቶች አንዱ የለውጥ መሳሪያዎቹ ከነባሪዊ ሁኔታዎች ጋር ተጣጥመው ያለመመረጣቸው ሲሆን ሁለተኛው የአመራሩና የሠራተኛው ለለውጥ የነበረው የባለቤትነት መጓደል ነዉ። ለዉጥ እንዲሳካ ለማድረግ ከአመራሩ ለውጥን ማቀድ፣ ርዕይ መቅረጽ፣ ግብ ማስቀመጥ፣ እሴት ማጎልበት፣ ስልት መንደፍ ፣ ሰራተኛውን አሳምኖ ማሰራት፣ ስልታዊ በሆነ መንገድ ችግሮችን መፍታትና ውሳኔ መስጠት ይጠበቅበታል። የሠራተኞችን፣ የአሰራርና የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን በጠንካራ ተቋማዊ ባህልና በባለቤትነት መንፈስ በመምራት እና ቀጣይነት ባለው ሁኔታ የለውጥ ግብ ስኬትን ማስመዝገብ የአመራሩ ቁልፉ ተልዕኮ ነው።

በመሆኑም እነዚህን ተግባራትና ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስፈልጉ ብቃቶችን የሚያረጋግጥበት ሥርዓት በትራንስፎርሜሽን እና በአገልጋይነት አመራር ሳይንስ እና ጥበብ መሳሪያዎች

አማካይነት የሚገነባ መሆን አለበት፡፡ ተቋማት የለውጥ አመራር ሳይንስና ጥበብን እንዲያጎለብቱ የሚከተሉትን ስትራቴጂዎች ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ዓላማ አድርጎ የሚከናወነው የሲቪል ሰርቪሱን ብቃት፣ ውጤታማነት፣ አካታችነት እና ዴሞክራሲያዊ የሆነ የአገልጋይነት ሥነ ምግባር በመላበስ ለተገለጋዩ ተገቢውን አገልግሎት በግልጽ የመመዘኛ መስፈርት መሠረት እየተገመገመ ውጤታማነቱ የሚታይበትና በተጠያቂነት መርህ መሠረት አገልግሎቶች በወቅቱ ለዜጎች መቅረብ አለባቸው፡፡ በመሆኑም ገቢር ነበብ የአመራር ሥርዓትን በመከተል የሲቪል ሰርቪስ የማሻሻያ ትግበራ ሥራዎች በአግባቡ መሬት ላይ እንዲወርዱ በማድረግ፣ ተቀማት የአገልግሎት አቅርቦት ውጤታማነትን እየመዘኑ፣ የአፈፃፀም ደረጃውን እያረጋገጡ መሄድ ያስፈልጋል፡፡

ተቀማት ከየሴክተራቸው ባህርይ ጋር በተጣጣመ መልኩ ተቋም ተኮር የሆኑ የአሰራር ማሻሻያዎችን፣ የአገልግሎት ስታንዳርዶች እና ስልቶችን የሚቀየሱበትና ለውጡን በፍጥነት ተግባራዊ የሚያደርጉበትን የትብብር እና ገቢር ነበብ የለውጥ አመራር ስትራቴጂን እንዲከተሉ ይፈለጋል፡፡ በህግ ኃላፊት የተሰጠው የተቋማዊ የለውጥ ትግበራ አስተባባሪ መስሪያ ቤትም (ስቪል ሰርቪስ ኮሚሽን) የህግ ማዕቀፍ በመቅረጽ፣ የመመዘኛ መስፈርቶች በማዘጋጀት፣ ለውጡ የሚመራበትን የአሰራር ሥርዓት በመንደፍ እንዲሁም ገቢር ነበብ የአመራር ሳይንስና ጥበብ በራሱ መስሪያ ቤት ላይ በመተግበርና ለሌሎቹ ተምሳሌት በመሆን ስራውን በተግባር እያሳየ እንዲያስተባብርና እንዲመራ ይጠበቃል፡፡

ተቋማት ዕጩ አመራር የሚፈራባቸው ወይም የሚከተከትባቸው ማሳዎች ናቸው፡፡ የአመራርነት ክህሎት በተቋማት ውስጥ በተጨባጭ ተግባር እንቅስቃሴ የሚፈጠር እና የሚዳብር ነው፡፡ ብቃት ያለው አመራር ሰጪነት የተጨባጭ ተግባራዊ እንቅስቀሴና የግል ጥረት ድምር ውጤት በመሆኑ ሲቪል ሰርቪስ ተቋማት በቂ የአመራር ሳይንስና ጥበብ እየገበየና በተግባርም እየተለማመደ ከሚሄደው የሰው ኃይል ውስጥ ለተለያየ የአመራር ቦታ ሊመደቡ የሚችሉ ጠንካራና ብቃት ያላቸውን ግንባር-ቀደም ዕጩ አመራሮች የማፍራት አሰራር በመዘርጋት የሚሰራ ይሆናል፡፡

2. ነፃ ገለልተኛ እና አካታች ሲቪል ሰርቪስ ለጠንካራ መንግስት ግንባታ

ነፃና ገለልተኛ ሲቪል ሰርቪስ ተቋም ማለት የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች ከማንኛውም የፖለቲካ፣ የብሔርና የጎሳ ውግንና፣ የጾታና ዕድሜ፣ የሀብት ደረጃ፣ የዝምድናና ጓደኝነት ትስስር እንዲሁም ከማናቸውም አገልግሎት አሰጣጥ ፍትሐዊነትን ከሚያጓድሉ አስተሳሰቦችና ድርጊቶች ነፃ የሆነ እና ተደራሽ አገልግሎት መስጠትን የሚያመላክት ነዉ፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የመንግስት ተቋማት ሁሉንም ኢትዮጵያዊያን በዚህ ማዕቀፍ እና ህጋዊ አሰራርን ብቻ ተከትለው እንዲያገለግሉ ኃላፊነት የተጣለባቸው ናቸው፡፡ በህግና በአሰራር መመሪያ ብቻ ተመስርተው የሚሰሩ ነፃና ገለልተኛ የመንግስት ተቋማትን መገንባት ፋይዳው ብዙ ነው፡፡

እነዚህ ተቋማት ለአገልግሎቱ የሚያስፈልገውን ቅድመ ሁኔታ ያሟሉ ኢትዮጵያንና በሀገሪቱ ህጋዊ ፍቃድ አግኝተው በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ላይ ተሰማርተው የሚገኙ የውጭ ሀገር ዜጎችንም ጨምሮ ፍትሐዊ፣ ግልፀኝነትና ተጠያቂነትን የሚያረጋግጥ አገልግሎት እንዲያገኙ ያስችላቸዋል፡፡ በዚህም ምርታማነታቸውን በማሳደግ በሚያገኙት ውጤት ትርፋማ ከመሆናቸውም ባሻገር ሀገራዊ ብልጽግናን ለማረጋገጥ በሚደረገው ጥረት ላይ የራሳቸውን አዎንታዊ አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ምቹ ሁኔታን ይፈጥርላቸዋል፡፡ ከዚህም ባሻገር በህዝብ ዘንድ አመኔታን ያተረፉ የመንግስት ተቋማትን በመገንባት በመንግስትና በህዝብ መካከል ጠንካራ መተማመንን ስለሚፈጥር በሀገረመንግስት ግንባታው ላይ የሚኖረው አዎንታዊ አስተዋጽኦም ከፍተኛ ይሆናል፡፡ እንደዚህ ዓይነት ነፃና ገለልተኛ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ሲገነቡ ቀዳሚው ትኩረታቸው ሀገርና ህዝብ ስለሚሆን በገዥ ፓርቲም ሆነ በሌሎች ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች በምርጫ ምክንያት ለውጦች በሚኖርበት ወቅት፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት እንቅስቃሴዎች ሳይስተጓጎሉ ወይም ትርጉም ያለው ጉዳት ሳይደርስባቸው የሚያስቀጥሉና የፖለቲካ አመረጋጋቱም ወደ ትክክለኛ መስመር ውስጥ እንዲገባ አዎንታዊ ተጽእኖ ማሳረፍ የሚችሉ የመንግስት ተቋማት እንዲገነቡ ያደርጋል፡፡

አሰራር ግልጽና ተጠያቂነት ያለው ለማድረግ የሚያስችሉ የህግና የፖሊሲ ማዕቀፎች ማዘጋጀትና አመራሩንና የመንግስት ሰራተኛውን ማሰልጠንና የጋራ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ፣ ዜጎችም መብትና ግዴታዎቻቸውን አውቀው የሚጠበቅባቸውን ቅድመ ሁኔታ አሟልተው ሲቀርቡ በተዘጋጀው የዜጎች ቻርተር መሠረት ተገቢውን አገልግሎት በፍትሐዊነት፣ በቅልጥፍና እና በተቀመጠው ስታንዳርድ መሠረት ማግኘት እንዲችሉ የማድረግ ግዴታ

እንዳለባቸው እንዲገነዘቡት ማድረግ ይገባል። ፖሊሲዎቹ አዋጆቹ፣ ህጎቹንና መመሪያዎቹን ሳይሸራረፉ ተግባራዊ እንዲሆኑ ስምምነት ላይ ከተደረሰ ህጎቹን በሚጥሱ ኃላፊዎችም ሆነ ሰራተኞች ላይ አስተማሪ የሆኑ የእርምት እርምጃዎችን ያለማመንታት እየወሰዱ ተጠያቂነትን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ አስተዳደር ጉዳዮች ማለትም ቅጥር፣ ዝውውር፣ ምደባና የደረጃ ዕድገቶች በህጉ መሠረት ብቻ መፈፀም እንዲሁም ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉና የአገልግሎት አሰጣጥ ቅልጥፍናን የሚያሳድጉ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች ጥቅም ላይ የሚውሉበትን ሥርዓት መዘርጋት ይገባል።

በዚህ ሂደት በስብጥር ረገድም ኢትዮጵያን የሚመስል ሲቪል ሰርቪስ ለመገንባት ዝርዝር ስትራቴጂና እቅድ ተዘጋጅቶ የሚተገበር ይሆናል። የተለያዩ ማህበራዊ መሠረቶች የሚያካትት ሲቪል ሰርቪስ እንዲሆን ታስቦ መሠራት አለበት። በሥራ ስምሪት ላይ የፖለቲካ ተመራጮችና ተሿሚዎች በህዝብ በተሰጣቸው ውክልና መሠረት ፖሊሲ የማውጣትና የመንግስት ሰራተኛው ለዜጎች ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው አገልግሎት መሰጠቱን የመቆጣጠር እና የማስተካከል መብት በሕገ-መንግስቱ በተቀመጠው አግባብ እንዲፈጽሙ ይደረጋል።

የመንግሥት አገልግሎት ሥራዎች የሚከናወኑት የዜጎች ምርታማነት ለማሳደግና የዴሞክራሲ ሥርዓት ለማስፈን መሆኑ ይታወቃል። አገልግሎቶቹን የሚሰጡ የመንግሥት ሠራተኞችም ሥምሪት የህዝቡ የተለያዩ ስብጥሮች ማለትም የብሔረሰብ፣ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የአካል ጉዳት...ወዘተ ያገናዘበ ሲሆን ለተገልጋዮችም የባለቤትነትና የበለጠ እምነት እንዲኖራቸው ያግዛል።

በኢትዮጵያ የሲቪል ሰርቪስ ውስጥ እነዚህን ስብጥሮች ከማረጋገጥ አንጻር ክፍተቶች ይስተዋሉበታል። በፌዴራል ሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ አንድ ሠራተኛ እንኳን የሌላቸው ወደ 15 ብሔረሰቦች አሉ። የሴቶች ድርሻ 38 ከመቶ ሲሆን የአካል ጉዳተኞች ምጣኔ ደግሞ 0.2 ከመቶ ብቻ ነው። የወጣቶች ምጣኔ ወደ 48 ከመቶ ድርሻ አለው። የኢትዮጵያን ሕዝብ ስብጥር የሚመስል ብዝሃነትና አካታችነት የሚያረጋግጥ ሲቪል ሰርቪስ ለመገንባት ስትራቴጂና ዕቅድ አዘጋጅቶ ወደ ተግባር መግባት ወቅቱ የሚጠይቀው አጀንዳ ነው።

ኢትዮጵያ በተለያዩ ብዝሀነት የምትገለጽ አገር ናት። ሲቪል ሰርቪሱም የኢትዮጵያን ብዝሀነት የሚያንጸባርቅ መሆን አለበት። ከዚህ በተጨማሪም በመንግሥት ተቋማት ውስጥ የሚከናወኑ የሰው ኃይል ስምሪት፣ የአገልግሎት አሰጣጥ፣ መረጃ እና ፍትህ የማግኘት እና የመሳሰሉት

ክንውኖች ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎች በአግባቡና በእኩልነት የሚያስተናግዱ መሆን ይኖርባቸዋል። ከዚህ አንፃር ብዝሀነትን ያረጋገጠ ሲቪል ሰርቪስ ደረጃ በደረጃ ለመገንባት በሲቪል ሰርቪስ ፖሊሲው የሚከተሉት የትኩረት መስኮች እንዲተገበሩ ተቀምጠዋል።

- የመንግሥት ሠራተኛውም ሆነ አመራሩ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት በውጤታማነት ሲፈጽምና ሲያስፈጽም ከማንኛውም ዓይነት የግል አመለካከትና ስሜት፣ ያልተገባ ጥቅም፣ ፖለቲካዊ ፍላጎቶች፣ ዝምድናና ጓዳዊ ግንኙነቶች ተጽዕኖ ነጻ ሆኖ፣ ብዝሃነትንና አካታችነትን አክብሮ ብቻ ሳይሆን ብቃቱንና ችሎታውን ሙሉ በሙሉ ተጠቅሞ አገልግሎት ስለመስጠቱ የሚረጋገጥበት አሠራር ይዘረጋል።

- የሰው ኃይል አስተዳደር ስምሪት ውስጥ የሠራተኞች ብዝኃነትና አካታችነት በሚጠበቀውና በሚቻለው ደረጃ ምጥጥን እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል።

- የሰው ኃይል አስተዳደር ሥምሪትና አገልግሎት አቅርቦት ስኬታማ እንዲሆን ብዝኃነትንና አካታችነትን የሚያረጋግጡ የህግ ማዕቀፎች እና ዕቅዶች እንዲቀረጹና እንዲተገበሩ ይደረጋል።

- የመንግሥት ተቋማት የትኞቹንም ምክንያቶች መነሻ አድርገው ከመለያየት ይልቅ ብዘሃነትን እና አካታችነትን ታሳቢ አድርገው፣ ልዩነታቸውንም አክብረውና የግል ማንነታቸውን ተቀብለው ለተቋማቸው ዓላማ መሳካት በጋራ የሚቆሙ የሠራተኞች ስብስብ እንዲኖራቸውና ተቋማዊ ባህልና እሴትን እንዲገነቡ እና አገልግሎቶችን በፍትሃዊነት እንዲያቀርቡ የሚያስችላቸው አሠራር ይዘረጋል።

- በሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ ነባር የሰው ኃይል አስተዳደር ሕጎችን በተገቢው መንገድ በማሻሻልና አካታች የሰው ኃይል ስምሪት ሥርዓትን በመፍጠር አካል ጉዳተኞች የሚኖራቸውን የተለያዩ ችሎታ፣ አቅምና ተሰጥኦ መጠቀም የሚያስችሉ አሠራሮች እንዲጠናከሩ ይደረጋል።

3. ሀገራዊ ተልዕኮን መሸከም የሚችል አደረጃጀት ለውጤታማ ዕቅድ አፈፃፀም መረጋገጥ

የሲቪል ሰርቪስ ተቋማት አደረጃጀት የሚፈጠረው የተቋሙን ተልዕኮ በብቃት ለመወጣት፣ አገልግሎትን በጥራትና በቀልጣፋነት በማቅረብ የዜጎች እርካታን ማረጋገጥ እንዲያስችል ነው። በሀገራችን የሲቪል ሰርቪስ ተቋማት አደረጃጀቶች ተፈጥረው አገልግሎት መስጠት ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ የሚፈለገውን ተልዕኮ ለመወጣት የተከናወኑ ተግባራት ቢኖሩም አሁን ከደረስንበት የእድገት ደረጃ አንፃር ሰፊ ጉድለት የሚታይባቸው ናቸው።

አንድ አቋም ጠንካራና ተልዕኮን መሸከም የሚችል ተቋማዊ አደረጃጀት አለው የሚባለው በህግ የተሰጠውን ተግባርና በኃላፊነት ታሳቢ ያደረገ መዋቅራዊ መጣጣም፣ ብቁ የሰው ኃይል፣ ውጤታማነትና ዘላቂነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ህጎችና አሰራሮች በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ተደግፎ ሲደራጅ ነው። በዚሁ መሠረት በበቂ ጥናት ላይ የተመሰረተ ፣ ሊያሰራ የሚችል እንዲሁም በየደረጃው ተናባቢ አደረጃጀት ፈጥሮ ለዜጎች ቀልጣፋ፣ ውጤታማ እና የህዝብ እርካታን የሚያረጋግጥ የሲቪል ሰርቪስ አገልግሎት የሚሰጥበት አሰራር ለመዘርጋት እና ሥራ ላይ ለማዋል የሚከተሉት ስትራቴጂያዊ ተግባራት ይከናወናሉ።

በነባሩ የሲቪል ሰርቪስ አሰራር ይስተዋል የነበረውን የአደረጃጀት ክፍተት ዝርዝር ጥናት በማድረግ ወዳልተማከለና የሴክተርን ባህሪ ወዳገናዘበ አለማእቀፋዊ አሰራር የሚቀየርበት ስርዓት ደረጃ በደረጃ እየተገነባ እንዲሄድ ይደረጋል። የትኛውም የመንግስት ተቋም አደረጃጀትና መዋቅር ከመፈጠሩ በፊት በባለሙያዎች አማካይነት አዋጭነቱ ላይ ዝርዝር ጥናት በማድረግ እና ውጤታማነቱ እየተገመገመ እንዲደራጅ ይደረጋል።

ፍትሐዊና ቀልጣና አገልግሎት ለዜጎች ለመስጠት እንዲቻል በፌደራል እና በክልል መንግስታት የተደራጁ ተቋማት አደረጃጀትና መዋቅር የሚያናበብ የሥራዎች ምድብ ስታንዳርድ (occupational classification standard) እንዲኖር ይደረጋል። በተጨማሪም በየአካባቢው የተመጣጠነ አደረጃጀት እንዲኖር የሚያስችል አሰራር ይዘረጋል። በተጨማሪም በየአካባቢው የተመጣጠነ አደረጃጀት እንዲኖር የሚያስችል አሰራር ይዘረጋል።

በዚሁ መሠረት በተፈቀዱ የሥራ መደቦች ላይ የሜሪት ሥርዓቱን ተከትሎ ስምሪት ለማካሄድ ለየሥራ መደቡ የሚቀመጡ ተፈላጊ ችሎታዎች ፣ ዕውቀት፣ ክህሎትና ባህሪይ ስታንዳርድን

መሠረት ተደርጎ እንዲለዩና ከሥራው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው የሰው ኃይል መለየት የሚያስችሉ ሆነው ይቀመጣሉ፡፡

የተቋማት አደረጃጀትና መዋቅር ለስራው በሚያስፈልገው የሰው ኃይል በመጠንም ሆነ በዓይነት እንዲሁም ተፈላጊ ችሎታዎች የያዘ መሆኑን መለየት የሚቻልበት ስርዓት በመዘርጋር የመንግስት አደረጃጀትና የክፍያ ሥርዓቱንም ከሀገሪቱ የመክፈል አቅም ጋር አገናዝቦ በማስተካከል አገልግሎት ማሳለጥ በሚያስችል አግባብ እንዲተገበር ይደረጋል፡፡

4. ብቁና ተወዳዳሪ የሰው ኃይል ማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት እንደ ቁልፍ የማስፈፀም አቅም ግንባታ

በአገራችን በሲቪል ሰርቪስ ተቋማት ውስጥ በቁጥር አነስተኛም ቢሆን የእውቀት፣ የተግባር ክህሎትና ልምድ እንዲሁም የአገልጋይነት መንፈስ እና ጥሩ ሥነ-ምግባር ያላቸው ሠራተኞች በመኖራቸው ለተገልጋዩ ህብረተሰብ ከነጉድለቱም ቢሆን ተቀማት የሚሰጧቸው አገልግሎቶች እየሰጡ ቀጥለዋል፡፡

በአንዳንድ ክልሎች አዲስ ሰራተኞችን በዩኒቨርሲቲዎች ፈተና በመስጠት የያዙትን የሥራ ብቃትና ችሎታ በመመዘን የመቅጠር፣ ከነውስንነቱም ቢሆንም አጫጭር ሥልጠናዎች የመስጠት፣ የሥልጠናና የትምህርት ዕድሎችን ከማበረታቻ ጋር ለማስተሳሰር ጥረት የሚያደርጉ ተቋማት መኖራቸው እንዲሁም አንዳንድ ተቀማት የሰው ኃይል ልማት መመሪያና የሥልጠና እቅድ አዘጋጅተው ሠራተኞችን በእውቀትና በአመለካከት እየገነቡ ለመሄድ የሚያደርጉት ጥረት መበረታታት ያለበት ነው፡፡

ይሁን እንጂ በአሁኑ ወቅት በሲቪል ሰርቪስ ውስጥ የሚገኘው አብዛኛው ሰራተኛ የብቃት ማረጋገጫ ሥርዓት ተገንብቶና ይህንኑ መሠረት በማድረግ የተሰማራ ባለመሆኑ ለበርካታ ተቋማት ግንባታቸውን በውጤታማነት ለማሳካት እንቅፋት ከመሆኑም ባሻገር የተገልጋዩን ፍላጎት በሚያረካ መልኩ አገልግሎት እየሰጠ አይደለም፡፡ በርካታ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ከአመራርና ከሰራተኞቻቸው ብቃት ጉድለት የተነሳ የሥራ እቅዶቻቸውን አሟልተው እየፈፀሙ አይደለም፡፡ በሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ ተሰማርተው የሚገኙት በርካታ አመራሮች እና ሠራተኞች ለተመደቡበት የሥራ ቦታ ውይም ኃላፊነት ከእውቀት፣ ከክህሎት፣ ባህሪና አስተሳሰብ አንፃር የሚፈለገው የማስፈፀም ብቃት ደረጃ የሚጎድላቸው በመሆናቸው የሚጠበቅባቸውን ተልዕኮ

በውጤታማነት መፈፀም እና በህግ የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት በሚፈለገው ደረጃ እያሳኩ አይደለም፡፡ በተለይም ችግሩ በሰራተኛው ዘንድ ከአመለካከት እና ከክህሎት አንፃር ጎልቶ የሚታይ ነው፡፡ በእውቀት ፣ በክህሎት እና በአመለካከት ብቃት ያላቸውና ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ ጥቂት ሰራተኞች ቢኖሩም አብዛኛው ሠራተኛ የብቃት ክፍተት ያለበት፣ ተነሳሽነት የሚጎድለው፣ በአብዛኛው የማሳበብ ባህርይ ጎልቶ የሚስተዋልበት በመሆኑ ብቃቱ ያላቸው በእነዚህ የሚዋጡበት ሁኔታ ይታያል፡፡

የመንግስት ተቋማት የሚጠበቅባቸውን ተልዕኮ መፈፀም እና በህግ የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት በሚፈለገው ደረጃ ማሳካት የሚችሉት ብቃት ያለው የሰው ኃይል በመሳብ፣ በስራ ላይ በማሰማራት እና ቀጣይነት ባለው መልኩ አቅሙን እያጎለበቱ መሄድ ሲችሉ ነው፡፡ በመሆኑም ውጤታማ የሰው ኃይል እቅድና ልማት ከተለዋዋጭ ሁኔታ ጋር ተጣጥሞ በተነደፈ እቅድ ላይ ተመስርቶ ሰውን የማልማትና የማዘጋጀት ስራ ቀጣይነት ባለው መልኩ የሚከናወንበትን አሰራር በመዘርጋት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

በዚሁ መሠረት አገራችን ከምትደርስበት የእድገት ደረጃና ከስትራቴጂያዊ እቅድ ጋር የተናበበ የተቋማት የሰው ኃይል እቅድ ዝግጅትና የመረጃ ሥርዓት የሚዘረጋ ይሆናል፡፡ በስትራቴጂክ እቅድ የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት የሚያስፈልገው የሰው ኃይል ፍላጎት ቅድመ ትንበያ በመስራት፣ በስትራቴጂክ ዘመኑ የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል መጠንና ዓይነት በእቅድ በመያዝ የመቅጠር፣ በአግባቡ የማዘጋጀት እና የመጠቀም እንዲሁም የሰራተኛውን ውጤታማነት በመከታተል እና በመገምገም የማስተካከያ እርምጃዎች የመውሰድ ስራዎች በተገቢው ሁኔታ የሚሰራ ይሆናል፡፡ ሁሉም የመንግስት ተቋማት የአዲስ ሰራተኞች ቅጥር በእቅድ በመያዝ የአጭር፣ የመካከለኛ እና የረጅም ጊዜ የሰው ኃይል ፍላጎት እቅድ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

ሲቪል ሰርቪሱ መንግስት ያወጣቸውን ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን በማስፈፀም ረገድ ቁልፍ ሚና አለው፡፡ ይህንን ሚናውን በሚፈለገው ደረጃ ለመወጣት የሰው ኃይሉ ብቃት እንዲኖረው ያስፈልጋል፡፡ የመንግስት ተቋማትን የተልዕኮ አፈፃፀም ውጤታማነትን ከማረጋገጥ አንፃር ለሰው ኃይል ብቃትና ምዘና ትኩረት በመስጠት፣ ግልጽነትና ተጠያቂነትን በሚያረጋግጥ ሁኔታ ብቃትን የመመዘንና የማረጋገጥ ስርአት በመዘርጋት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ በዚህም የሰው ሀብት አስተዳደርና ልማት ሥራዎች ብቃትን መሠረት በማድረግና የሜሪት ሥርዓትን በመከተል የሚከናወኑ ይሆናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአዲስ ሰራተኛ ቅጥር፣ እድገትና ማትጊያ

የሚፈጽመው በሚዘረጋው የብዝሃነትና የአካታችነት ስትራቴጂ፣ እቅድና የምዘና ሥርዓት መሠረት በውድድሩ በሚረጋገጠው ውጤት መሠረት ይሆናል።

በስራ ላይ ያለው የመንግስት ሰራተኛ በስራው ላይ የሚቆየውም ሆነ በደረጃ እድገት እና በሙያ እድገት መሰላሉ ስርዓት ተጠቃሚ የሚሆነው ሁሉም ሰራተኛ በቅድሚያ በምዘና ስርዓቱ ገብቶ ማለፍ ሲችል ነው። በሂደቱም አሁን ያለው የመንግስት ሰራተኛ በአራት አርጅ የመክፈል እድል ሊኖረው ይችላል። የመጀመሪያው በምዘና ሂደቱ ሲያልፍ ለተመደበበት የሥራ መደብ ብቃቱን የሚያረጋግጥ፤ ሁለተኛው የተወሰነ የብቃት ከፍተኛ የሚስተዋልበትና በሞጁላር ስልጠና ሊያሟላና ቀጥሎም በምዘናው ብቃቱ የሚረጋግጥ፣ ሶስተኛው ለተመደበበት የሥራ መደብ ያለበት የብቃት ክፍተት ስፋት ያለውና በመደበኛ ትምህርት እንዲሟላ የሚጠበቅ ሲሆን አራተኛው ደግሞ በምዘና ሂደቱ ለተመደበው ሥራ ያለው ብቃት ዝቅተኛ የሆነና በስልጠናም ይሁን በመደበኛ ትምህርት ክፍተቱን ለማሟላት የሚቸገር የሰው ኃይል ነው። ከዚሁ ሂደት የሰው ሀብት ልማቱ ቀጣይነት ያለው እንዲሆን በስራ ላይ ያሉ የመንግስት ሰራተኞችን ብቃት ለማጎልበት የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ፣ ክፍተታቸውን በመለየት በዕቅድ ላይ የተመሠረተ የብቃት ክፍተት ማሟያ ስልጠናዎች በስፋት የሚሰጥበት አሠራር ሥርዓተ ይከተላል።

5. የተገልጋይን እርካታ ያረጋገጠ የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት ለፈጣን ልማት መረጋገጥ

የአገልግሎት አሰጣጥን በቅርበት በቴክኖሎጂ ጭምር እየተከታተሉ የሚፈጠሩ ችግሮችን በአፋጣኝ ለመፍታት እየሰሩ ያሉ የመንግስት ተቀማት እና ኃላፊዎች እንዳሉ ይታወቃል። ከአመራር አገልጋይነት ጋር ተያይዞ አመራሩ በኃላፊነት መንፈስ ሥራዎቹን በቅርበት እየተከታተለ በሚመራባቸው ተቋማት ውስጥ ሰራዎችን ተረድቶ ለአገልግሎቶች ስታንዳርድ እንዲዘጋጅ እያደረገ ከተቋሙ ሰራተኞች ጋር በተቀናጀ መልኩ አገልግሎት መስጠት የጀመሩ መኖራቸው የሚበረታታ ተግባር ነው። ከዚህ አኳያ ተገልጋዩ ህብረተሰብ ማሟላት የሚገባውን ቅድመ ሁኔታ ሲያሟላ በዜጎች/በተገልጋዮች ቻርተር በተቀመጠው ስታንዳርድ መሠረት አገልግሎት እየሰጡ ያሉ የተቋማት አመራሮችና ሠራተኞች መኖራቸው የመንግስትን ስራ በተቀናጀ መልኩ ለመምራትና ተግባራዊ ለማድረግ የተቀመጠውን አቅጣጫ ወደ ተግባር እየተቀየረ መሆኑን የሚያመላክትና ተቀምሮ መስፋት የሚገባው መልካም ተግባር ነው።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ተገልጋዮች በመደበኛ ሥራቸው ላይ እንዳሉ የሚፈልጉትን አገልግሎት ማግኘት እንዲችሉ የኦንላይን አገልግሎት መስጠት መጀመሩና ውጤትም እየታየበት ያለ ሲሆን

የተገልጋዮችንም እንግልት የሚቀንስ እንደሚሆን ይታመናል። በተጨማሪም ተያያዥነት ያላቸውን አገልግሎቶች የሚሰጡ ለአብነት ውልና ማስረጃ፣ ገቢዎች ያሉ ተቋማትን የአንድ መስኮት አገልግሎት እንዲሰጡ መደረጉ ተገልጋዩን ካላስፈላጊ ወጭና እንግልት የሚታደጉ መሆናቸው እሙን ነው። የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣንም የኤሌክትሮኒክስ የመንግስት ግዥ ስርዓት በመገርጋት የመንግስት ተቋማትና የንግዱ ማህበረሰብ ባሉበት ሆነው መገበያየት እንዲችሉ ማድረግ መቻሉ በተሞክሮነት የሚወሰድ ዘርፌ ብዙ ተቀሜታ ያለው ተግባር ነው። በአንዳንድ አካባቢዎችና ተቋማት ያለውን ችግር በመረዳት ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ ህገወጥ ተግባራትን በሚፈጽሙ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ላይ አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃዎች ለመውሰድና ተጠያቂነትን ለማስፈን እየተደረገ ያለው ጥረት መልካም ጅማሮ የሚባል ነው።

ከላይ የተገለጹ ጥንካሬዎች እንደተጠበቁ ሆነው በሀገራችን በየደረጃው ባሉ በመንግስት ተቋማት ውስጥ እየተሰጡ ያሉ አገልግሎቶች የተለያዩ ውስብስብ ችግሮች የሚታዩባቸው ናቸው። አብዛኞቹ የመንግስት ተቋማት በተለይም ለአብዛኛው ዜጎች አገልግሎት በሚሰጥባቸው ደረጃዎች ያለው የሥራ አካባቢ ለአገልግሎት ሰጪውም ሆነ ተቀባዩ ሳቢና ምቹ አይደሉም። አንዳንዶቹ የመንግስት መሥሪያ ቤቶች ከመግቢያ በራቸው ጀምሮ በሰው ጉልበትና በአነስተኛ ወጪ እጅግ ውብና ሳቢ ማድረግ እየተቻለ ለተገልጋዩ ማራኪ ሳይሆኑ ይታያሉ። መፀዳጃ ቤቶቻቸው ምቹ ካለመሆናቸውም ባለፈ ጤና ላይ ችግር ሊያስከትሉ የሚችሉ ናቸው። በአብዛኛው አካባቢ ለህዝብ አገልግሎት ለመስጠት የተመደበው ሰራተኛ የሚቀመጥበት በቂ ወንበርና ጠረጴዛ ባለመኖሩ አንዱ በሌለው መቀጫ ወንበር ላይ በየተራ እየተቀመጠ እንደሚያስተናግድ የሚገደድበት አካባቢ ረዥም ሰዓት ቆይቶ ለህብረተሰቡ አገልግሎት መስጠት እንዳይችል ከማያደርጉ ምክንያቶች አንዱ ነው።

በሰራተኛውም ዘንድ የሚፈለገውን አገልግሎት ለመስጠት የእውቀትና የክህሎት ማነስ፣ ትጋትና ተነሳሽነት አለመኖር፣ ለተገልጋዩ ተገቢውን አገልግሎት ከማቅረብ ይልቅ ለራሱ ፍላጎት ቅድሚያ መስጠት፣ አገልግሎቶችን ለጥቅም መደራደሪያ ብሎ ማዘግየት፣ ተገልጋይን ማመላለስ፣ እንዲጨነቅና አማራጭ እንዲያጣ በማድረግ ማበሳጨት በየደረጃው ባሉ የመንግስት ተቋማት ውስጥ በስፋት ይታያል። ከአመራር ሹመት እስከ ሰራተኛ ቅጥር ያለው ሂደት በአንዳንድ አካባቢዎች በገንዘብ፣ በጓደኝነት፣ በዝምድናና በመሳሰሉት ትስስሮች ይፈፀማሉ። በዚህ መልኩ የሚገቡ አመራሮችም ሆኑ ሰራተኞች ለሚመደቡበት ቦታ፣ ለሚሰጣቸው

ተግባርና ኃላፊነት የሚያበቃቸውን አግባብነት ያለው የብቃት ማለትም የዕውቀት፣ የክህሎት፣ የአስተሳሰብ እና የሞራል ዝግጁነት ስለማይኖራቸው ለተገልጋዩ የሚፈልገውን አገልግሎት መስጠት አይችሉም።

አገልግሎት ተጠቃሚውም መብትና ግዴታውን በአግባቡ መረዳት ላይ ክፍተቶች ስላሉበት አገልግሎቶችን በገንዘብ እየገዛ እንደሆነና በዚህም ምክንያት የሚያማርረው የህብረተሰብ ቁጥር እየጨመረ ሄዷል። ይህ ማለት አገልግሎቱን ማግኘት የሚችለው ገንዘብ ያለው አሊያም አገልግሎቱን ሊሰጥ በሚችለው ተቋማም ውስጥ ዘመድ፣ ጓደኛ ወይም ሌላ የግንኙነት ሰንሰለት ያለው ተገልጋይ ስለሚሆን ህብረተሰቡ በመንግስት ተቋማት ላይ ያለውን የባለቤትነት ስሜት እየቀነሰ መጥቷል። የእነዚህ ሁሉ ምንጫቸው የስብዕና መጓደልና የሞራል ውድቀት ነው። ይህ ሁኔታ ከለውጡ በፊት በነበረው ሥርዓት ሀገራችንን ለከፍተኛ ቀውስ ከዳረጉት ምክንያቶች አንዱ እና ተጠቃሹ መንስኤ ነው። በዚህ ምክንያት በየተቋሙ ከፍተኛ የአገልጋይና የተገልጋይ እንግልትና እሮሮ ይታያል። የአገልግሎት ሰጪውንና ተቀባዩን አካላዊ ግንኙነት በመቀነስ ሌብነት ይቀንሳል ተብሎ ተስፋ የተጣለበት የኦንላይን አገልግሎት መስጠት ያልጀመሩ በርካታ ተቋማት መኖራቸው ለችግሩ መባባሳት አስተዋጽኦ አድርጓል። ስለሆነም እነዚህን ችግሮች በዘላቂነት ለመፍታት የሚያስችሉ እርምጃዎችን በፍጥነት መውሰድ ያስፈልጋል። ሌላው ከአገልግሎት አሰጣጥ አኳያ የሚታየው ችግር አመራሩም ሆነ ሰራተኛው በሥራ ሰዓት በሥራ ቦታ ተገኝቶ አገልግሎት ያለመስጠቱ ጉዳይ ነው። በሠራተኛውም ዘንድ በተገብው ሰዓት በሥራ ገበታው ላይ ተገኝቶ አገልግሎት የመስጠት ችግር በስፋት እንደሚታይ መረጃዎች ያሳያሉ። ጧት አርፍኦ መግባት፣ የገባውም ቢሆን የሰዓት መፈረሚያው ላይ ፊርማውን ካሳረፈ በኋላ ወዲያው ጥሎ መውጣት፤ አንዳንድ አካባቢዎች ተቋማት ውስጥ ያሉ ሰራተኞች ደግሞ ከሰዓት በኋላ ጨርሶ ሥራ የማይገቡ መሆኑ በተወሰነ ደረጃ በተደረጉ የዳሰሳ ጥናቶች ተረጋግጧል።

ተቋማት የአገልግሎት አሰጣጣቸው እየተመዘነ ህዝቡ እንዲያውቀው የሚደረግበት እንዲሁም እንደየዘርፉ ባህሪ የሚሰጡ አገልግሎቶች ጥራትና ደረጃ በዓለም አቀፍ የጥራት ስራ አመራር መመዘኛዎች መሠረት የሚገመገሙበት ሥርዓት ይዘረጋል። የአገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል ዓለም የሚጠቀምባቸውን ምርጥ ልምዶች በመውሰድና ከየዘርፉ ባህሪ ጋር በማጣጣም አገልግሎቶች ጥራት ያላቸው ፣ ቀልጣፋና ተደራሽ እንዲሆኑ ይደረጋል።

በአጠቃላይ በመንግስት ተቋማት ውስጥ ያሉ አገልግሎት አሰጣጥ ሲታይ ከጥንካሬዎቹ ይልቅ ጉድለቶቹ በእጅጉ የገዘፉ ናቸው፤ ይሁን እንጂ ሊስተካከል የማይችል ችግር አይደለም፤

የሚያስፈልገው ልክ እንደቀደሙት አባቶቻችን እና እናቶቻችን ወቅቱ የሚጠይቀውን ዋጋ ለመክፈል አመራሩ እና ሠራተኛው ችግሩን መፍታት እንደትውልድ ተልዕኮ ወስዶ በአንድነትና በቁርጠኝነት መንፈስ መወሰድ ብቻ ነው፡፡ የኛ ቁርጠኝነት እንደአባቶቻችን የህይወት መስዋእትነትን አይጠይቅም፡፡ ከንዋይ ምርኮኝነት ነፃ ሆኖ ፣ በንጹህ ህሊና፣ በሀገር ፍቅር ስሜት፣ ለትውልድ ታማኝ ባለአደራ በመሆን ተግቶ በመስራት የህዝብን ፍላጎት የሚያረካ አገልግሎት መስጠት ብቻውን ረጅም መንገድ ሊወስደን ይችላል፡፡ ይህንን በእጃችን ባለን ሰብዓዊና ቁሳዊ ሀብት ብቻ እና ያለምንም ተጨማሪ ኢንቨስትመንት ማሳካት እንችላለን፡፡ ስለዚህ መላው አመራሮችና ሰራተኞች የሁኔታውን አሳሳቢነት በመረዳት ይህንን ሀገራችንና ህዝባችንን አመራሮችና ሰራተኞች የሁኔታውን አሳሳቢነት በመረዳት ይህንን ሀገራችንና ህዝባችንን በዘላቂነት የሚቀይር ሥራ መሥራት ለነገ የምንወዝፈው ሳይሆን ዛሬውኑ ተግባራዊ በማድረግ ለተጀመረው ለውጥ ዳር መድረስ ያለንን ጽናት በተጨባጭ የምናሳይበት መለካም አብነታዊ ተለዕኮ ነው፡፡

6. ውጤትን የሚመዝን የሥራ አፈፃፀም አመራር፣ ተነሳሽነት ለሚፈጥር የማትጊያ ሥርዓት ግንባታ

የሥራ አፈፃፀም አመራር ሥርዓት ስትራቴጂያዊ የልማት ግቦችን በየደረጃው ላሉ ፈፃሚ አካላት በመከፋፈል የሚታቀድበት፣ ለትግበራው ግብዓት የሚመደብበትና የሚቀናጅበት ፣ እቅዱ የሚተገበርበት፣ አፈፃፀም የሚለካበት፣ የመልካም አፈፃፀምና ጉድለት እውቅናው ሆነ የተጠያቂነት ሥርዓተ የሚሰፍንበት የሥራ አመራር መሳሪያ ነው፡፡ የስራ አፈፃፀም አመራር ስርዓት ዓላማውን ፈፃሚና አስፈፃሚውን የሰው ኃይል በተፈላጊው እውቀት፣ ክህሎት እና አስተሳሰብ በመገንባት ብቁ ፣ ውጤታማ እና ቀልጣፋ ሲቪል ሰርቪስ በመፍጠር ለህዝቡ ሙያዊ ስነ-ምግባርን በጠበቀ ሁኔታ አገልግሎት እንዲሰጥ ለማድረግ ነው፡፡

በመሆኑም ሁሉም የመንግስት መስሪያ ቤቶች የአገራችን ሲቪል ሰርቪስ የሥራ አፈፃፀም ምዘና ሂደትን መሠረት የሚያደርግና ከተቋም ውጤት ያልተገናዘበ ከመሆኑም ባሻገር የውጤት ግሽበት የሚስተዋልበት ነው፡፡ መንግስታችን ያስቀመጣቸውን የልማት እቅዶች አፈፃፀሙን በመከታተል፣ በመገምገምና ትክክለኛ የምዘና ውጤት የመስጠት አሰራር በመዘርጋት አፈፃፀሙን በቅርብ መከታተል ይገባል፡፡ የመንግስት ሥራ ከተቋም፣ ከሥራ ክፍልና ከፈፃሚ ሥራ ጋር ተሳስሮ የሚታቀድበት፣ በፀደቀው እቅድ መሠረት በተለዩ ቁልፍ የውጤት አላካቾች

አማካይነት የሚገመገምበትና የሚመዘንበት የአፈፃፀም ሥራ አመራር ማዕቀፍ በማዘጋጀት በሁሉም የመንግስት መሥሪያ ቤቶች የሚተገበርበት ሥርዓት ይዘረጋል።

የሥራ እቅድም ሆነ አፈፃፀም ከሰራተኛ እና ከስራ ክፍል፣ ከተቋም እና በአገር ደረጃ ከሚጠበቅ ውጤት ጋር የሚሰናሰል፣ ቁርኝትና መናበብ ያለው መሆኑ እንዲረጋገጥ ይደረጋል። ስራ ከአገር እና ከተቋም ስትራቴጂያዊ እቅድ በመነሳት የሚታቀድበትና የሚተገበርበት፤ በየደረጃው ያለውን የስራ ክፍሎችና የሰራተኞችን የስራ አፈፃፀም ምዘና በተጨባጭ መለኪያዎች እና ውጤቶች አንፃር ክትትል የሚደረግበት፤ የሚገመገምበትና የሚመዘንበት ፣ እርስ በርሱ የተናበበ እና የአፈፃፀም አመራር ኡደቶችን አሟልቶ በሚጠቀም ማእቀፍ የሚመራበትን ስርአት ተከትሎ የሚፈፀም ይሆናል። በኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ የተደገፈ የሥራ እቅድ የአፈፃፀም ምዘና በየደረጃው በማካሄድ አመራሩን፣ በየደረጃው ያለውን የሰው ኃይልን እና ተቋማትን በየጊዜው በመገምገም የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ይደረጋል።

ለመንግስት ሰራተኞች የሚሰጥ እውቅናም ሆነ ተጠቃቂነትን በቀጥታ ከእቅድ አፈፃፀም ውጤት ጋር የተያያዘ እንዲሆን ይደረጋል። የስራ አፈፃፀም ምዘናው ግልጽ፤ ተጨባጭ መረጃን መሰረት ባደረገ መልኩ አፈፃፀምን ለመለካት የሚረዱ ዝርዝር መስፈርቶች እና ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾችን በማዘጋጀትና በየወቅቱ በማሻሻል ሰራተኛውን በመመዘን፣ የላቀ አፈፃፀም ውጤት ያስመዘገቡ ሰራተኞችን የሚያበረታቱ እንዲሆን ይደረጋል። እንዲሁም ክፍተት የታየባቸውን ደግሞ ተገቢውን የእርምት እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል አሰራር የሚዘረጋ ይሆናል። በዚህ መሰረት የሥራ ምዘና ውጤት ከብቃት ምዘና፣ ከደመወዝ ጭማሪ፣ ከደረጃ እድገት፣ ከጥቅማጥቅምና ከእውቅናና ማበረታቻ ጋር የሚቆራኝበት እና ጠንካራ ሠራተኞች በሲቪል ሰርቪሱ የሚቆዩበት ደካሞች ደግሞ ከሲቪል ሰርቪሱ የሚወጡበት የአሰራር ሥርዓት ይገነባል።

7. የዲጂታል ሲቪል ሰርቪስ ለዘመነ የመንግስት አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ

አለማችን ከደረሰችበት ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ሲቪል ሰርቪስ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የማዘመን፣ ዲጂታላይዝ የማድረግ እና ተግባራትን በኦንላይን የማስፈፀም አሰራር ሥርዓትን መከተል ብቸኛ መፍትሔ መሆኑን ማመን ያስፈልጋል። የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ የመንግስት መኖር እና በግባቡ ተግባሩን እይፈፀም ስለመሆኑ አስተማማኝ መሠረት የሚጥል ነው። የቴክኖሎጂ አጠቃቀማችን ስናሳድገው የሲቪል ሰርቪሱን የአገልግሎት አሰጣጥ እንድንወደው ፣

በግልጽ መረጃዎችን እና አገልግሎቶችን እንድናገኝ፣ እንዲሁም ወደ መንግስት ተቋማት ስንሄድ ምቾት እንዲሰማን የሚያደርግ ይሆናል።

የዲጂታል ሲቪል ሰርቪስ የመገንባት ሂደት በሀገራችን እጅግ ወደኋላ የቀረ መሆኑን በመገንዘብ በቀጣይ በመንግስት የሚሰጡ አገልግሎቶችን ቅልጥፍናና ጥራት እንዲሻሻል፣ ተቋማት በኔትዎርክ እንዲተሳሰሩ፣ የዲጂታል ሲቪል ሰርቪስን በማልማት ደህንነቱ የተረጋገጠና ቀጣይነት ያለው አገልግሎት መስጠት የሚችል ሥርዓት መገንባት ዋነኛ ዓላማው አድርጎ የተነሳ ነው።

ለዚህም ያዝማ ዘንድ በዚ ስር የሚከተሉትን ዋና ዋና የፖሊሲ ግቦች ተቀርጸው ወደ ስራ እንዲገቡ ይደረጋል።

የሲቪል ሰርቪስ አገልግሎቶችን የሚደግፉ የሲስተሞችንና ፕላትፎርሞችን እንዲሁም አገልግሎቶቹን አቀናጅቶ የሚያቀርብ የፖርታል ዝርጋታን ማጠናከር፤ ደህንነታቸው በተጠበቀ የኔትወርክ እና የአገልግሎት ማቅረቢያ መተግበሪያዎች የማልማት እና የማስፋፋት ሥራዎች ይሰራሉ። የሲቪል ሰርቪስ ተቋማትን የሚያስተሳስር የመረጃ ቅብብሎሽን የሚያጠናክር የኔትወርክና የመሠረተ ልማቶች ዝርጋታን የሚፋጥን፣ የዲጂታል ዳታቤዝ ይገነባል። የመረጃ ማደራጀት፣ ትንተና እና የሪፖርት አቀራረብ ሥርዓትን በማጠናከር ፤ የመንግስት ሰራተኞችን መለያ የመታወቂያ ቁጥርን ግምት ውስጥ ያስገባ የሠራተናኞች መረጃ ዳታቤዝ ልማትን መገንባት የሚሉ ግቦች በቁርጠኝነት እንዲሳኩ ርብርብ የሚደረግባቸው ይሆናል።

ሀገር የተሻለ ደረጃ እንድትደርስ ይህ ስራ ለነገ የሚባል ስራ አይደለም። ኋላቀር አሰራርን መከተል የእውቀት እና ክህሎት ክፍተት መገለጫ ብቻ ሳይሆን አሁን ባለንበት ዓለም የንግድ ልንጠቀምበት የሚገባ ቴክኖሎጂ ነው። በመሆኑም በዚህ ወቅት በየደረጃው ያለው አመራር እና ሰራተኛ በመጀመሪያ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ዙሪያ ራሱን በማብቃት ቀጥሎም በዙሪያው ያሉትን እና ተቋሙን በማዘመን ተወዳዳሪ የአገልግሎት አሰጣጥን እውን ማድረግ አለብኝ ብሎ በቁጭት መንፈስ ወደ ስራ ሊገባ ይገባል። ምክንያቱም ኢትዮጵያም በአለም ላይ ያሉ በጎ ነገሮች ሁሉ ይገባታል፣ ያስፈልጋታልም። ከሲቪል ሰርቪስ አኳያ የሀገራችን ልኳ በቴክኖሎጂ የዘመነ እና ተግባራትን በፍጥነት ፣ በጥራትና ከሌብነት በፀዳ አግባብ የሚፈጽም ተቋም መገንባት ነው።

8. ውጤታማነትን የሚያሳድግ የክፍያና የማበረታቻ ስርዓት ለምርታማነት መሻሻል

በኢትዮጵያ ያለው የክፍያ ሁኔታ ሀገራችን ካለችበት የኢኮኖሚ ሁኔታ ጋር በተያዘ የክፍያ ስርዓቱ ከውጤት ጋር ያለመያያዙ ብቻ ሳይሆን የክፍያ መጠኑም እጅግ ዝቅተኛ የሚባል ነው።

በሌላ በኩል ሲቪል ሰርቪሱ በዚህ ወቅት ያለበት ሁኔታ ሀገር ከምትጠብቀው የማስፈፀም አቅም በታች ሆኖ ይታያል። ከላይ በዝርዝር ለማየት እንደተሞከረው ለውጥን የሚመራ ብቁ የሆነ አመራር እጥረት፣ ዘርፉን የሚመጥን ብዛት እና ብቃት ያለው የሰው ኃይል ውስንነት፣ ብልሹ የሆነ የአገልግሎት አሰጣጥ፣ ወጪ ቆጣቢ እና ውጤታማ ያልሆነ አደረጃጀትና አሰራር፣ ሳይንሳዊ ያልሆነ የሥራ አፈፃፀም የምዘና ዘዴ፣ የሥራ ውጤትን መሠረት ያላደረገ የክፍያና ማትጊያ ስርዓት እንዲሁም በአግባቡ በቴክኖሎጂ ያልተደገፈ አሰራር በመኖሩ ለተገልጋዩ እና ምርታማነት የሚጨምር እርካታ የማፈጥር አገልግሎት እየሰጠ አይደለም።

በዚህም መነሻነት ውጤታማነትን ከፍ የሚያደርግ የክፍያና የማበረታቻ ሥርዓት መገንባትን ትኩረት ያደረገ በጥናት ላይ የተመሠረተ፣ ከብቃትና ከስራ አፈፃፀም ጋር የተሳሰረ የሰሪተኛን ውጤታማነት የሚያበረታታ የደመወዝ፣ የማትጊያና የማበረታቻ ስርዓት መዘርጋትና ተግባራዊ ማድረግ ይገባል።

በጥረት በሚገኝ ውጤት መሠረት የሚፈፀም የደመወዝ ክፍያ፣ የእርከን ጭማሪ፣ የማትጊያና የማበረታቻ ሥርዓት መዘርጋትና ትግበራውን ማጠናከር እንዲሁም የሥራ ደረጃ ዕድገት መሰላል ከብቃትና ከደመወዝ ጭማሪ ጋር ያስተሳሰረ ስርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊም ይደረጋል።

ማጠቃለያ

በሀገራችን የመንግስት መስሪያ ቤቶች ተቋማት ይዘት ያለውን አገልግሎት መስጠት ከጀመሩ ረዥም ዓመታትን አስቆጥረዋል። እነዚህ ተቋማት ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማትና ዕድገት እንዲሁም ለዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ አዎንታዊ ሚና ተጫውተዋል። የመንግስት ቢሮክራሲያዊ አሰራር በዘመናዊ ህግና አመራር የተደራጀና አገልግሎት የሚሰጥ፤ በሳይንሳዊና ዓለማቀፋዊ ሥርዓት መሠረት እንዲገነባ በማድረግ ሀገራችን ወደ ዘመናዊ ሀገረ-መንግስት ሥርዓት ግንባታ ውስጥ እንድትገባ አግዟል። የመንግስት ተቋማትን የመፈፀም አቅም ከማሻሻል አኳያ የህግ ማዕቀፎችን እንዲሁም የአሰራር ሥርዓቶችን እና የአደረጃጀቶችን አቅም ለማሳደግ የሚያስችሉ በርካታ የለውጥ ሥራዎችን ለማከናወን ጥረት የተደረገ ሲሆን እነዚህም በሲቪል ሰርቪሱ የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም ላይ መሻሻሎችን አምጥተዋል። በየደረጃው ያሉ

መዋቅሮች በአደረጀጀታቸውም ሆነ በአገልግሎት አሰጣጣቸው ብዝሃነትን እና አካታችነት አገናዝቦ በመሥራት ረገድ ብዙ የሚቀር ነገር ቢኖርም ኢትዮጵያን የሚመስሉ ተቋማትን ለመፍጠር እስከ አሁን የተደረገው ጥረትና የመጣው ለውጥ በተለይ በክለሎች በመልካም ጅምርነት መወሰድ የሚችል ነው። ከነጉድለቱም ቢሆን በሀገሪቱ ለመጣው ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ልማትና እድገት ጉልህ አስተዋጽኦ አበርክተዋል።

ይሁን እንጂ እነዚህ ተቋማት በእድሜያቸው ልክ አደረጃጀታቸው በህግና አሰራር ፣ ብቃት ባለው የሰው ሀይልና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የህዝቡ የእድገት ፍጥነትና ፍላጎት ማስተናገድ የሚችሉና ከፍተኛ ተለዋዋጭነት (dynamism) ባለው ዓለማቀፍ ሁኔታ ውስጥ የተወዳዳሪነት አቅም ያላቸው ሆነው የተገነቡ አይደሉም። አብኖውን ጊዜ ተቋማቱ ጠንካራና ሀገርን ተሸክሞ በየትኛውም የፖለቲካ ሥርዓትና ሁኔታ ውስጥ የማስቀጠልን ጉዳይ ሳይሆን የገዥ ፓርቲን ስልጣን ከማስንበት አኳያ ስለሚቃኙ ለጠንካራ መንግስት ግንባታ ያበረከቱት አስተዋጽኦ በጣም አነስተኛ ነበር። አገልግሎት አሰጣጣቸው የገለልተኝነት፣ የቅልጥፍና፣ የፍትሐዊነት እና ተያያዥ ችግሮች ያሉበት በመሆኑ እያደገ የመጣውን የተገልጋዩን ህዝብ ፍላጎት የማርካት ችግር ያለባቸው ናቸው። ውጤታማነት እንዲያሻሽሉ በየጊዜዉ በመንግስት ተቋማት ውስጥ ተግባራዊ የሚደረጉ ሪፎርሞች ከመጠነኛ ለውጥ ባለፈ የሚፈለገውን ውጤት ማምጣት እና ጠንካራ መንግስት መገንባት አልቻሉም። ሪፎርሞች እና የአመራር ግንባታ ሥርዓት ቅኝቶች በመርህ የሚመሩ፣ ሀገርንና ህዝብን ያስቀደሙ፣ ሪፎርሞቹን መርተው ውጤታማ ማድረግ የሚችሉ እንዲሁም ቀጣይነት ያለውን ልማትና ብልጽግና ማረጋገጥ የሚችሉ ተቋማትን ከመንባት ይልቅ የፖለቲካ ተልዕኮን ለማስፈፀም ቅድሚያ የሚሰጡ ሆነው ዘልቀዋል።

ቀደም ሲል የነበረው የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም በሚፈለገው ደረጃ ውጤት አላስመዘገበም። በዚሁ ምክንያት ከአምስት ዓመት በፊት ለውጡ እንደተጀመረ ሲቪል ሰርቪሱ እና መላው የአገራችን ሕዝብ የሪፎርም ዝለት ሰለባ እንደሆነ በግልጽ መቀመጡ ይታወሳል። ለዚህም የአመራሩ የቴክኒካል አቅም ክፍተት፣ የሪፎርም መሳሪያዎቹን እንደ የፓርቲ ፖለቲካ መሳሪያዎች የማየት አዝማሚያ፣ የማትጊያ ሥርዓት ያለመዘርጋት፣ ለሁሉም ተቋማት አንድ ዓይነት የለውጥ መሳሪያ እንዲተገበር ማስገደድ የመሳሰሉት ችግሮች ተጠቃሽ ምክንያቶች ሆነው መለየታቸው ይታወቃል።

በዚህ የለውጥ እንቅስቃሴ በአደረጃጀቱ ጠንካራ፣ ብቁ በሆነ የሰው ኃይል የተሟላ ፣ ግልጽና ተጠያቂነት ህግና አሰራር ያለው፣ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደራጀ ሲቪል ሰርቪስ በመገንባት

የጀመርነውን ሀገራዊ የብልጽግና ጉዞ ከዳር ለማድረስ መረባረብ ይበጠቅብናል። ይህ የህዝቡን ሁለንተናዊ ብልጽግና ከማረጋገጥ ባሻገር ኢትዮጵያን የአፍሪካ የብልጽግና ተምሳሌት ለማድረግ ያስቀመጥነውን ርዕይ ለማሳካት የማይተካ ሚና ይኖረዋል። ስለሆነም በመንግስት በኩል ተዘጋጅተው እንዲተገብሩ የወጡ ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞችና እቅዶች ውጤታማ ሊሆኑ በሚችሉበት አግባብ መምራት፣ መፈፀምና ማስፈፀም የሲቪል ሰርቪሱ ቁልፍ የአርበኝነት ተልዕኮ ይሆናል። በሂደቱም ጠንካራ መንግስት የመገንባት ግባትን ይሳካል።